# የቡችላውም ይወገድ፤ የሰጎኑም ይቅር፤ የዕብድ ውሻውም ያክትም

ሀማ ቱማ

በዘመነ "ድንቄም ፖለቲካ!" ደርሰናልና ዝብርቅርቁም፤ፈጣጣውም፤ ታች አብሽ የወረደውም ማለትም የዘቀጠውም ጊዜ የሰጠው ቅል ሆኖ በመድረክ ሲንጎማለል ማየቱ የግድ ሆኖብን ትግላ ችን እንጥስ ቢሉ ቅንጥስ ዓይነት ሆኖ መጠቀ ስንል እየወደቀ፤ ጠነከረ ስንል እየደከመ አረመኔ ቡድንን 18 ዓመት መታቀፍ ዕጣ ክፍላችን ሆኗል፡፡ ትግል ነውና፤ ታጋይም ነን እንላለንና፤ የለውጥ አማርኛ የወፍ ቋንቋ አልሆነብንምና፤ ትግል የምንለው ለይስሙላ ሳይሆን የልብና የእምነ ት በመሆኑ ጨለምተኝነት ሊያንበረክከን ባለመቻሉ፤ ሕዝብ ያቸንፋልን በማስቀደም፤ የድል ቀን መምጣቱን በማመን ቀቢፀ ተስፋ ሆድ አምላኩ እንዳያረገን መንገዱን ዘግተንበት ቆመናል፡፡ ግን ፈተናው ቀላል አይደለም፡፡ የደከሙትና የንጋትን--የጎህን ቅንድብ ማየት ያቃታቸው ደግሞ ጀግንነትና ሀገር ወዳድነትን በተለጣፊነትና በወያኔ ቡችላነት ለውጠው የፖለቲካ አመንዝራነትን ና የውርደትን ማቅን መከናነብ ተገደዋል፡፡

ፖለቲካ በተለይም የሀገራችን ፖለቲካ የፏለለ ጊደርም ሳይቀር የሚፈነጭብት የመሰላቸው ከታሪክ መማርን ንቀው፤ ጥራዝ ነጠቅነትንና ግብዝነትን ተጫምተው፤ሀይልና ስልጣን ከሕዝብ መስረፁን በመፃረር፤ ነፍጥ ያነገበውና ንዋይን ዘርፎ ያካባተው የደም ዙፋን ባለቤት ሁሉ ስዩመ መለኮት እየመሰላቸው ለጣዖት የሚሰግዱ የሚከተሉት የቡችላ ፖለቲካ ነጋ ጠባ ሀገራችንን ሲፈታተን ቆይቷል፡፡ ዕድሜህን ያርዝመው እንደ ማቱሳላ፤ ፀሀዩ ንጉሳችን ወዘተ ብለው ይጮሁ የነበሩት ሎሌዎች ብልሁ ሊቀመንበር፤ ቆራጡ የጦር መሪ ወዘተ እያሉ ሞት ሞት ድንፋታን ሲያሰሙ በነበሩት ተተክተውና ጨለማውም አልነጋ ብሎ ተራና ቆሻሻ ጠባብ ቡድንን የሚመራን ከሀዲ የሚያሞግሱ ከርስ አምላኩዎች ሀገሪቷን ሲያምሷት ዓመት በዓመት ተተክቶ ፍትህን ፍለጋ ው እየተደናቀፈ ከዛሬ ደርሰናል፡፡ እያንዳንዱ የጨቀየ ስርዓት የራሱን ትልና ዝንብ እየፈለፈለ በሕዝብ ላይ ፈንጭቷል፡፡ የቡችላ ፖለቲካ ሀገርን አጠፋ ብንል የተጋነነ አይሆንም፡፡ የዚህ ፖለቲ ካ ዋና መለያው ላለው ስርዓት መጎንበሱ ነው፡፡ ምክንያቶቹ በእርግጥ ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ሥዩመ እግዚአብሔር ናቸውና አፄውን መፃረሩ ሐጢያት ነው ሊባልም ይችላል፡፡ አብዮተኛ መሪያችን ነውና መታዘዝ አለብንም ተደምጧል፡፡ ነፃ አውጪ፤ ዕድገት አምጪ፤ ብሄረሰባችንን ጠቃሚ የሚሉም አሉ፡፡ በዚህም በዚያም ግን ቡችላዎች ለጌታቸው ይጮኃሉ፡፡ ለሆድ መገዛትን፤ ፍርሀት ን ማንገስን ያቀፈ የፖለቲካ ምርጫ ነውናም  ውርደቱን ሸፋፍኖ ማቅረብ ይገደዳል፡፡ ጥቅሜና ፍርሀቴ አሸነፈኝ ማለቱ  ቅሌት መሆኑን መረዳት ቡችላውም አይጠፋውምና መደበቂያ ሰበብ ይፈልጋል፡፡  ሰላማዊ ትግል ይቅደም፤ ጦርነት ያብቃ በሚል ትጥቅ ያስፈታል፡፡ ቀሰ በቀስ ዕንቁላ ል በእግሩ ይሄዳል በሚልም የገማና የተባለሸ ዕንቁላል መቸም በእግሩ ሊሄድ አለመቻሉን ይደብ ቃል፡፡ ፀጥ ብለን እንገዛ፤ ተንበርክከን እንታገል፤ ጠላትን ወዳጅ እንበለው፤ ሁላችንም አንድ ነን ወዘተ በሚል ጅብና አህያን ተኩላና በግን ሊያፋቅርና ሊያጋባ ደፋ ቀና ይላል፡፡ በኢትዮጵያ

ታሪክ የቡችላ ፖለቲካ አቀንቃኞች ብዙ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ የወኔ እጥረትን በምላስ መንጣጣት
ም ሸፍነዋል፡፡ ብልህ ነን፤ ስልጡን ነን፤ እውነታውን ተገንዝበናል በሚልም ዕይታቸውን በፍርሀታ
ቸው ጋርደው ቆራጥ ትግልን ያኮላሻሉ፡፡ በዘመናዊ ጦር ታጥቆ የመጣውን ፋሺስት ጦር ልጋፈጥ
ማለት ሕዝብን ማስጨረስ ነው ሲባል አልነበረም? ባንዳነት አልተቀነቀነም? አርበኞች በችኩልነ
ት፤ በዕብደትና ሕዝብን በማስጨረስ አልተወገዙም? ፍርሀትና ክህደት በብልህነት ጭምብል
ጀርባ ተደብቀው የቪቫ ዱቼ ቪቫ ግራዚያኒ የቅሌት ጩኸት በሀገራችን ታሪክ ውስጥ አሳፋሪ
ምዕራፎችን አስፍሮ አልፏል፡፡እነ በላይ ዘለቀና ታከለ ወልደ ሐዋርያት ዓይነቶቹ ባይኖሩ ኖሮ
የነ ኃይለ ስላሴ ጉግሳ ዓይነቶቹ ቡችላነትና ባንዳነት ባቸነፈ ነበር፡፡

እንታዘብ ካልን አንድ ዜጋ እንዴት ውድ ሀገሩን ይከዳል፤ እንዴትስ የወገኑ የስቃይ ጩኸት ከመ
ብራቅ ሲያስተጋባ ጆሮውን ይደፍናል ብሎ መጠየቁ አይቀሬ ይሆንብናል፡፡ ሰው ከእንስሳ የሚለየ
ው በህሊናው ነው ካልን ደግሞ ሰው ነኝ የሚል ግለሰብ እንዴትስ ህሊናውን ገድሎ ቀፎውን
ቀርቶ  በወንድሙና እህቱ ስቃይ ላይ ደስታውን ይገነባል ብለን መጠየቅ እንገደዳለን፡፡ ላለው
ቅንጭብ ያረግዳል በተባለው መሰረት ለጉልበተኛው ሰጋጅ ብዙ ነው ብለን መደምደም አለብን?
ወይስ አንድ አወቅኩ ባይ ግለሰብ እንደለፈፈው ባህላችን ለባርነት ይዳርገናል? የአንበሳን ኑሮና
ክብር አስትቶ ቡችላ ያደርገናል? በዚህ አቅጣጫ ሊደረግ የሚችለው ግምገማ እንዳለ ሆኖ
በቅድሚያ  ፍርሀትን ለማሸነፍ አለመቻላችን በሀላፊነት ተጠያቂ መሆኑ ይታያል፡፡ ትግል
መራራ ነው፤ እምቢታ ከኃያላኑ ወይም ባለነፍጦቹ ቁጣን ቅጣትን ያስከትላል፡፡ ለሀገር መቆም
መታገል መስዋዕትነትን ጠያቂ ሲሆን ፍርሀትን አሰተናግዶ ፊሪ ለእናቱን አስተጋብቶና
“ መበርከት ብልጠት ” መፈክርን አሰምቶ ከትግል መራቁ--አንገት ደፍቶ አፍን ዘግቶ--መገዛቱ
ሊመረጥ ይችላል፡፡ ለነገሩ ፈሪና ደፋሩ የሚለየው ደፋሩ መቸም ቢሆን መቼ ሞትን ባለመፍራቱ
ሳይሆን ለክቡር ዓላማ በመታገሉ ፍርሀትን በማቸነፉና ሞት አይፈሬ መሆን መቻሉ ነው፡፡
የጣሊያን ወራሪን በጦር ጋሻና አልቤን ገጥመው የተሰዉት፤ የተሰቀሉት፤ ጭንቅላታቸው የተቆረ
ጠው ጀግና አርበኞች ሆኑ በፋሺስት ደርግ አረመኔዎች ስየል ሲቀበሉና በውድቅት ሲረሸኑ እናቸ
ንፋለንን ያሰሙት ጀግኖች ሁሉ በዓላማቸው ያመኑና ቃል ኪዳናቸውን ያከበሩ በመሆናቸው
ሞት ሊያስፈራራቸውና ሊያሸንፋቸው አልቻለም፡፡ ስለዚህም ለገዢዎች ሁሉ ቡችላ ላለመሆን
ከተፈለገ በዓላማ ማመንና ፍርሀትን ማሸነፍ የግድ ይሆናል፡፡ በውርደት ከመኖር ክብርን ጠብቆ
ማለፍ መሻሉን ማመንም ያስፈልጋል፡፡

ባህላችን ለባርነት ይዳርገናል ብሎ እስከመሳሳት ባንገፋም በፖለቲካው መስክ የታየውና የታለፈ
ው ታሪክ ለቡችላነት ፖለቲካ ጥርጊያ ማደላደሉን መካድ ግን አይቻልም፡፡ ባንዳው ሲሾምና
አርበኛው ሲሰቀል ይህ ያስተላለፈው መልዕክት ለሀገር መታገል ክቡር ነውን ሳይሆን ያስጠቃልን
ነው፡፡ ባንዳው ብልጥ አርበኛው ሞኝ ተደርጎ ተወሰደ ብንል ስህተት አይሆንም፡፡ ጎርፉ ሲመጣ
ለሸ ብሎ ማሳለፍ፤ ለሙሶሊኒም አድሮ፤ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ሁሉ ጎንበስ ጎንበሱን
አጧጡፎ መበርከት ነው ብልጠት የሚለው ትምህርት በስርዓቱ ተላላፈ ፡፡ ከበላይ ዘለቀ እስከ

ታከለ ወልደ ሀዋርያት ለሞት ሲዳረጉ ባንዳው ግን አለፈለት። ይህ የታሪክ ምፀት አድርባይነትና ግለኝነትን ከማስፈን አንፃር ከፍተኛ ሚና ነበረው፣ ዛሬም አለው። በዘመነ ደርግ መሰዋዕት የሆኑ ትና እናት አባታቸውን አለጧሪ ትትው ያለፉት፣ ልጆቻቸውን እርግፍ አድርገው ትተው የሞትን ፅዋ የጠጡት ጀግኖች በመከበር ፈንታ በ “ አለቁ” ተፈርጀው፣አርአያነታቸው ተክዶ፣ በዚያ በቀውጢ ትግል ጊዜ ግን ከአገዛዙ ጋር ተሞዳሙደው ሆነ ለስለስ ጎንበስ ብለው ህይወታቸውን ያተረፉት ሲመሰገኑና ሲደነቁም ታዝበናል። ልጆቼን ተቆጥቼ ስላሳደግኩ ወደ ትግል ሳይገቡ አንዳቸውም ሳይሞቱ ይኸው አሜሪካ ጠርተው እየጦሩኝ ነው ያሉ አንድ አባት የዚህን ቅሌት ይዘት በንግግራቸው ገልጠዋል። የትግል መራራነት የሚታገሉትን ሲያሰቃይ የዳር ተመልካች ብቻ ሳይሆን ከፀረ ሕዝቡ አገዛዝ ጋር ያበሩትና አልፎም በወንጀል የተሳተፉት ግን በተለምዶ አነጋጋር አልፎላቸው ወይም ቢያንስ ህይወታቸው ተጠብቆ መገኘቱ ቡችላነትን ብልጠት አስመስሎ አቅርቦታል። ሆዳም ሀገር የለውምናም የግል ጥቅማቸውን ብቻ ያስቀደሙት ዜጎች ለገዢውሀይል ቡችላ እየሆኑ የሕዝብን ትግል ሲጎዱ ቆይተዋል። ቤት መሬት እንመራ፣ በንግድ እንሰማራ፣ ከወያኔ ጠጋ ብለን ፍርፋሪ እንቃርም የሚሉት ሳያፍሩ መድረክ የሚያጣብቡት ይህ ባንዳን ርኩስና ውጉዝ ከመ አርዮስ ይል የነበረው ልምዳችን በመበረዙ መሆኑ ግልፅ ነው። የአሰፋ ማሩና የተስፋዬ ታደሰ ልጆች ጠባቂ አባት አጥተው፣ ከአፄው ጊዜ ጀምሮ በትግል በጫካም በእስ ር ቤት ሲጠበሱ የነበሩት እነ ጋይም ተሰውተው፣ እነ ፀጋዬና ይስሐቅ ደብዛቸው ጠፍቶ፣ እነ ፕሮፌሰር አሥራትም ለከርቸሌና ለሞት ተዳርገው፣ የምርጫ ድምፃችን ተቀማ ያሉት ተገድለው ና በሺም የሚቆጠሩት ታግተው ወዘተ ባለበት ቡችሎቹ ግን ፓርላማ ሲገቡ፣ በንግድ ሲሰማሩ፣ ፎቅ ቤት ቪላ ሲሰሩ፣ ልጆቻቸውን በልዩ ትምህርት ቤቶች ሲያስተምሩ፣ ሲንደላቀቁ፣ አልፎላቸ ውና ቀብጠው በህዝብ ላይ ሲፏልሉ የሚያይ የአዲሱ ትውልድ አባል የቡችላነት ፖለቲካ ያዋጣ ቢመስለው ልንፈርድበት አንችልም። ከዚህ ባሻገር ደግሞ ትግሉ መራራና ረጅም ሆኖ ሲገተር ልባቸው የሳሳና ወኔያቸው በእማዬ ድረሺልኝ የተተካ ሲሆን ኮረፍታው ዳሸን፣ ፎገራውም ገደል መስሎ ይታያቸዋል። በቃን በቃን ከበሮ በልባቸው ሲደለቅ ይህን በልዩ ልዩ ሰበቦች አጅለውና ሸፋፍነው የስልጡንነት፣ እውነታን የመገንዘብ፣ ፅንፈኝነትን የመተው፣ ጦርነትን የመሰልቸት፣ አቅምን የማወቅ ነፀብራቅ ነው በሚል ለአገዛዙ ቡችላ ይሆናሉ። በአሁኑ ጊዜ በየድርጅቱ የፈሉት አንጃዎችና ለወያኔ ተለጣፊ ለመሆን ሩጫ የያዙት ተስፋ ቢሶች በሞላ የዚሁ አሳፋሪ ቡችላነት ነፀብራቆች ናቸው።

የቡችላነት ፖለቲካ ሰለባዎች በርከት ሲሉ በሌላ በኩል ደግሞ ከትግላችን አንፃር ጎጂ ሆኖ ያለው በሽታ ደግሞ የሰጎን ፖለቲካ የተባለው መሆኑ አያከራክርም። ሰጎን ከጠላቶቿ ስትሸሽ አንገቷን በአሸዋ ውስጥ ቀብራ አዳኞቿን ካላየች የሚያዩዋት አይመስላትም። ችግርን የለም በማለት ተኖ እንዲጠፋ ማድረግ ይቻላል የሚለው ቅዠት በፖለቲካው መስክ በጣም ጎጂ ነው። የነበረው ስርዓ ትን ፀረ ሕዝብነት በመካድ ለምን ለውጥ አስፈለገ ለሚለው የሚሰጠው መልስ አልባሌ ከሆነ የዛሬንም ጋሬጣ ማወቅና መቋቋም ከቶ የሚቻል አይሆንም። የአፄው ስርዓት ለብዙሀኑ መከራና ስቃይ ነበር። ዴሞክራሲያው አልነበረም፣ እኩልነት አልነበረም። በዚያን ጊዜ የነበሩ ታጋዮችና

ለውጥ ፈላጊዎች ለነበሩት ችግሮች መፍትሄ ፈለጉ እንጂ ዛሬ በአንዳንዶች እንደሚባለው ችግሮቹን እንደ አስማት ሰሪ ከአየር አልሰረጿቸውም:: በኢትዮጵያ የተከሰተው የኤርትራ ችግር፣ የብሄረሰቦች ጥያቄ በተራማጆችና በኢሕአፓ የተፈጠረ ሳይሆን ከነበረው አገዛዝና ስርዓት የተወለደ መሆኑ ግልፅ ነው:: የሰጎን ፖለቲካ አቀንቃኞች ግን የነበረውን ስርዓትና መዘዙን ማየትን ትተው ለውጥ ያሉትን ማውገዙን ይመርጣሉ:: የመንግስቱ ኃይለ ማርያም አረመኔያዊ አገዛዝ ሀገር ወዳድና ሀገር ገንቢ ነው ብለው የሰፈነውን ግፍ አናይም ይሉ የነበሩ ጥቂት አልነበሩም:: እስከ ዛሬም ቢሆን የዚያን አረመኔ አገዛዝ ወንጀል ደብቀው ሰለባውን በጥፋተኛነት ሊወነጅሉ የሚጥሩ አሉ:: ሀገር አጥፊው ወያኔ ለስልጣን ሲበቃም በሀገራችን ላይ መዓት መጣ ብሎ ኢሕአፓ ሲጮህ ሰሚ ብዙ አልነበረም:: ተማሪዎች ይህን ቡድን ተቃውመው ሲሰለፉና ሲገደሉ የሰጎን ፖለቲካ አቀንቃኞችና የወያኔ ቡችሎች አብረው፣ ወያኔን ልጆቼ እያሉ፣ ሲያሳዝኑ እያሉ፣ጊዜ እንስጣቸው እያሉ የሀገርን ጠላት ደግፈዋል:: የሰጎን ፖለቲካ መለያው ያለውን ሀቅና እውነታ አላይ ብሎ በባዶ ምኞትና ተስፋ ብቻ መንጎዱ ነው:: ሊበሏት የፈለጓትን አሞራ ቃና ያለው አቅዋምም ነው፡ የሰጎን ፖላቲካ ጀሌዎች ሀቁ መራራ ስለሚሆንባቸው ምኞታቸውን ማቀፉን ይመርጣሉ:: ይህ ግን ስህተት ነው:: ሀገር አድን ትግሉ መራራውንም ሀቅ መገንዘብን የግድ ይላል:: ከስሜታዊነት በመራቅ ተጨባጭ ሁኔታውን--ኮሰውን በተለይ--መገምገም ያስፈልጋል:: ይህ ከተደረገ ጠላትና ወዳጅን በሚገባ መለየት ይቻላል:: ራስን ማሞኘትና መደለል አይበጅምና የሰጎን ፖለቲካ ወይም የውድ መታወሩ ነገን አያሳይም:: ዛሬ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ የተነሳ መሆኑ ግልፅ ሆኖ ሳለ ይህን ሀቅ  አልቀበል ብሎ መጃጃሉ ሀገርን ለባሰ አደጋ የሚያጋልጥ መሆኑ መታወቅ አለበት::

ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ስንገመግም በአካባቢያችን ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሀገራችን ጣውንቶችና ጠላቶች እነማን መሆናቸው ግልፅ ሊሆን ሲገባ የሰጎን ፖለቲካ ያይልና ኢትዮጵያ ትጥፋ ባዮችን ኢትዮጵያን ያድኑ ዘንድ ስንለምን ስንማጠን ታይተናል:: የወያኔ አገዛዝ በሰላም ላይወገድ፣ የመለስ ቡድን በምርጫ መቼም ተሸንፎ ስልጣን የማይለቅ መሆኑ ደም ፈሶ የተፃፈ ሀቅ ሆኖ ሳለ ዛሬም በምርጫው ቧልት ገብተን ጮቤ እንርገጥ ባዮች አሉ:: የወያኔን የበላይነት ተቀብለን ከተገኘን፣ ከተጎነበስን ህጋዊነት ተለግሰን መንቀሳቀስ እንችላለን ብለው የሚቃዡ  አንጃዎች አሉ ::መሰሪ ጎረቤቶች  ለነፃነት ትግል ይረዱናል ብለው የሚሞኙም ጥቂት አይደሉም:: አውቆ የተኛ ቢቀስቅሱት አይነቃ እንደተባለው ሁሉ የሰጎን ፖለቲካ ደቀመዝሙሮች ዓይናቸውን ይሁነኝ ብለው ዘግተዋልና የቀትርን ፀሐይ ማየት አይችሉም:: የሀገር ህልውናን ለማስጠበቅ ሁኔታው ግድ ካለ ያለፈን ቂምና ቁርሾ ወደ ጎን ማስቀመጡ ተገቢ ቢሆንም የትላንት ወንጀለኞችን የዛሬ አርበኞች ማድረግን በተመለከተ የሰጎን ፖለቲካ መርሳትን ቢያነግስም ለትግል ጠቃሚ አይደለም :: ትላንት  በሕዝብ ላይ ወንጀል ሲፈፅሙ የነበሩት፣ ጦርነት ልንሰራባችሁ ነው ያሉን፣ በትግራይ መሬት ነፃ ጋዜጦች አይገቡም ብለው የከለከሉት፣ አማርኛ ብናገር ሽቅብ ይለኛል--ኦሮሞ መገንጠል አለበት ሲሉ የነበሩት፣ ከደርግ ጋር በቀይ ሽብር የተሳተፉት፣ መለስን ደግፉ ብለው የጮኹት፣ በብሄረሰብ መደራጀት መከፋፈልን የደገፉት፣ የሕዝብን አድማ ያከሸፉት፣ ወዘተ

ሁሉ ንስሃ ሳይገቡ አጠፋን ሳይሉ ከመ ቅፅበት አርበኛ ጀግና የሚባሉበት ሁኔታ ሊቀጥል የሚገባ አይደለም፡፡ ይቅርታ ከሕዝብ ይጠየቅ ማለቱ ቂምና ቁርሾን ውሀ ማጠጣት ሳይሆን ወንጀለኛው ጥፋቱን አምኖ ይቅር ሳይባል ከሕዝብ ጎራ መግባቱ ጎጂ በመሆኑ ነው፡፡ በደፈናው ነፃ አውጪ የሚባለው የትላንት ወንጀለኛ  ነፃነትን ሊያመጣ መቼም አይችልም--ትግልን ግን ያደናቅፋል፡፡

የቡችላ ፖለቲካ ቅጥረኛነትን፣ የሰጎን ፖለቲካ ታውሮ መገዛትን የሚያስከትሉ ሲሆን የእብድ ውሻ ፖለቲካ ደግሞ ከግራ ቀኙ አናክሶ ጠላትን አብዝቶ ለውድቀት ይዳርጋል፡፡ እብድ ውሻ አላፊ አግዳሚውን ሊነክስ እንደሚቃጣው ሁሉ የእብድ ውሻ ፖለቲካ አቀንቃኞች ጠላት ወዳጅ ሳይለዩ ሁሉንም ለማደባየት ሲቅበዘበዙ ይታያሉ፡፡ ይህ ሁሉንም የመንከስ ሆነ የማንቋሸሽ ፖለቲካ በመሰረቱ ጠቀሜታው ለወያኔ መሆኑ ብዙም አያከራክርም፡፡ በተለይ ተቃዋሚ ሀይሎች አይረቡም ወዘተ በሚል የሚካሄደው የማጣጣል ዘመቻ ለሀገር ተቆረቆርን በሚሉትም ቢቀርብም መጨረሻው ሕዝብን ተስፋ አስቆርጦ ማንሳፈፍ ነውና ተጠቃሚው ወያኔ ብቻ ነው፡፡ ካለን ተመክሮ ስንነሳ ድረጅቶችን መተቸት በኃጢያት ደረጃ እየተፈረጀ ያለ በመሆኑ የእብድ ውሻ ፖለቲካ ስንል ተገቢውን ትችት ከማቅረብ ጋር አለመያያዙን ማቅረብ ተገቢ ይሆናል፡፡ ድርጅቶችን በስራቸውና መስመራቸው የተነሳ መተቸት አለባቸው፡፡ ለምን ተነኩ፣ የሹም ዶሮ ናቸውና ተደፈሩ የሚለው በፖለቲካው መስክ ቦታ የለውም፡፡ በአንድ በኩል የሆነ ጣዖት ያቆሙና በሌላ በኩል ደግሞ ቀሪውን ሁሉ አዋርደው የሚጥሉ እብድ ውሻዎች በፖለቲካው መስክ መድረክና ሜዳ ካገኙ ጉዳቱ ከፍተኛ ነው፡፡ ከገደል የሚከት የዝንጀሮ መንገድ ነው፡፡ ድርጅቶችና መሪ ነን የሚሉትን በአግባብ የመተቸት መብት ሊገደብ የሚችል ባይሆንም በፀረ ወያኔ ድርጅቶች ላይ እንደ እብድ ውሻ መናከሱ ጠቃሚና ገንቢ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ትኩረታችን በወያኔ አገዛዝ ላይ መሆን አለበት የሚለው ጥሪ ወቅታዊ የሚሆነው፡፡ የእብድ ውሻ ፖለቲካ ግን ማን ጠላት ማን ወዳጅን የለየ ባለመሆኑ ግራ ቀኙን እየነከሰ ለአገዛዙ ጠቃሚ ሆኖ ይሰለፋል፡፡ ዛሬ ወያኔ ላይ ሳይሆን የጭቃ ጅራፋቸው በተቃዋሚ ሀይሎች ላይ የሆነው ክፍሎች የዚህ አጥፊ ፖለቲካ አራማጆቸ ናቸው፡፡ ራሳቸውን ፀረ ወያኔ ማለታቸውም ሚናቸውን አይቀይረውም፡፡ እብድ ውሻ ጭራውን  ቢቆላም እብድ ነው፡፡ በመሆኑም ድክመት ቢኖራቸውም ፀረ ወያኔ ሆነው የሚንቀሳቀሱትን ድርጅቶች በትኩረት የሚያጠቁና የሚያብጠለጥሉ ለሀገራዊ ትግል ጠቃሚ ሳይሆኑ ጠንቅ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ አግባብ ያለው ሂስን ከዘለፋ እንድንለይ የግድ ይላል፡፡ ድርጅቶችና የድርጅት መሪዎችን ማን  ነክቶ የሚሉት በአንድ ጎን ያሉ ሲሆን ሁሉንም አዋርዶና ነክሶ ማልፈስፈስ የሚሉ ደግሞ በሌላ ፅንፍ ይሰለፋሉ፡፡ በሁለቱ መሀል  ጤነኛው ሚዛን ይገኛል፡፡ ይህ ግን ከእብድ ውሻ ፖለቲካ ፣ ከሁሉንም ንከስ ግደል ፖለቲካ የተለየ ነው፡፡

ለሀገሩ ህልውናና ለመስረታዊ መብቱ የሚታገል ሕዝብ ከፅንፈኛ የፖለቲካ አቅዋሞችና አማራጮች መራቅ አለበት፡፡ ከመነሻው መድረሻው ይታወቃል ነውና ገና ከጠዋቱ ትግል ለምን፣ ትግል ማንን ተቃውመን፣ ትግል ለምን ግብ የሚለውን በግልፅ ማወቅ አለብን ማለት ነው፡፡ የመደናበር ጉዞ በትግል መስክ ወደ መጥፎ ገደል የሚከት ነው፡፡ ለሀገር ታግለውና ከፍተኛ

መስዋዕትነትን ከፍለው መከራን የተቀበሉ ድርጅቶችን ዛሬ ሊያክችለችሉ የተነሱ ክፍሎች ሊረዱት ያልቻሉት  ወይም አውቀው ችላ ያሉት የካዱት ሀቅ ግን ለሀገር መሰዋት ክብር ነው የሚለውን ነው፡፡ ሀገሬ ወገኔ ብለው ተሰልፈው ሞትን የተጋፈጡትን ሰማዕት የሚነቅፉቱ ዛሬ ለሀገር እንሰዋ ጥሪን ቢያስሙ አዳማጭ ማጣታቸው አያስገርምም፡፡ ብልጠትና ስልጡን ፖለቲካ የተባለው በመሰረቱ ትግል እርሜን አንጋሽ ሆኖ በመቅረቡና የታገሉት አለቁ ፣ ያታገሉት አስጨ ረሱ በመባላቸው ለሀገርና ለወገን መሰዋቱ ባለማወቅ ተፈርጆ ፣ ይሉኝታና መጠቀም ባንድ አይገኝ ሰፍኖ፣ ዛሬ ህይወቴ ለሀገሬ ባዩን ከሞኝ የሚፈርጁ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ የታገሉ ትርፋቸ ው ስቃይና መከራ ሲሆን መስለው የኖሩትና ከአገዛዞች ያበሩት ዛሬ ያለፈላቸው የደላቸው ሆነው መገኘታቸው የሚሰጠው መልዕክት ታገሉ የሚል አለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ባንወደውም አለሁ የሚለን ሀቅ በመሆኑ ልናስወግደው ከተነሳን የሀገራችንን የጀግኖችና የመስዋዕትነት ታሪክ ማስተጋባትና ማስፈን እንዳለብን ግልፅ ይሆናል፡፡  ታሪክ ቅርስ ነው ግና የሕዝብ ትጥቅ ሆኖ እንዲያገለግል ከተፈለገ በሕዝብ መታወቅ አለበት፡፡ ይህ ደግሞ የታሪክ በራዦችን መታገል ያስፈልጋል ባይ ነው፡፡ የቅኝ አገዛዝ ለአፍሪካ ጠቅሟል የሚሉ ጉዶች በአሁኑ ጊዜ ፈልተው እንዳሉት ሁሉ እንጀራ ከሚበሉት ፓስታ በላተኞች ይበልጥ ስልጡን ናቸው ያሉንም እንዳሉ መርሳት  የለብንም፡፡ ታሪክ ስንልም ሀቁን እንጂ የፈጠራውን ሊሆን አይችልም፡፡ የሀገራችን ታሪክ መቶ ዓመት አልሞላውም የሚሉን አሉ፡፡ ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ናት ባዮችም አሉ፡፡ ሌላም ሌላም፡፡ የደርግ አገዛዝ ሕዝብን በሽብር ፈጅቶ እያለ ይህን ክደው የታገሉት ሀይሎች ሕዝብን አስጨረሱ ብለው ሊከሱ የሚጮሁም አሉ፡፡ ወያኔ ሀገርን እያጠፋ የለም ሀገሪቷን አሳደገ ጠቀመ ብለው የሚቀጥፉም ብዙ ናቸው፡፡ ከአፄ ዘመን ጀምሮና ከዚያም በደርግ አገዛዝ ታጋዮች የከፈሉ ትን መስዋዕትነት በተመለከተ የሀሰት ታሪክ ተራኪዎችን በመቃወም ሀቁን ማስከበር ዜጋዊ ግዴታ ነው፡፡ ለባለጌ ገድሉ ውርደቱ ቢሆንም ለሀገር ወዳዶች በተቃራኒው ገድላቸው ለሀገርና ለወገን የከፈሉት ዋጋና መስዋዕትነት ነው፡፡ ሀገራችን ታሪክ አላት-- ይህን ማስከበር ያስፈልጋል፡ ፡ ታሪክና ቅርስን ለማስከበር ደግሞ ህዝባዊና ሀገራዊ መንግስት መኖሩ ወሳኝና ተቀዳሚ ነው፡፡ ማለትም ለሀገርና ለሕዝብ መታገሉ ቀዳሚ ግዳጅ ነው ማለት ነው፡፡

ሁልጊዜ ከመጮሄ የተነሳ ዝም ባልሁ ጊዜ አጥንቴ ተበላሸ ያለውን የዳዊት መዝሙር መድገም ያልፈለግን በየጊዜው ስንጮህ ያተረፍነው ውግዘት መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሀገራችን ለአደጋ ተጋልጣ ባለበት የግል ቁስልና ብሶት ቦታ የሚሰጠው ሊሆን አይችልም፡፡ እብድ ውሾች ሊናከሱ ቢጥሩም ተከላክለን ሀቁን ማስተጋባት አለብን፡፡ ሀገር ሲጎዱና ሲያደሙ እያየን ልንተች ስንቃጣ በክብረ ነክ የከሰሱን ነበሩ፡፡ ግን ሀገር ከሁሉም በላይ ናትና ከሀገር ጥቅም አንፃር እገሌ ይቀድማል ብለን አፋችን ሊሸበብ አይገባውም፡፡ ሀቁን በድፍረት መገምገምና ማቅረብ ካልቻልንማ ሀሳዊ መሲሆች ና አስመሳዮች መድረኩን አጣበውና ብዙሁኑን አደናግረው ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ ዛሬ ነጋ ጠባ አላፊ አግዳሚውን መድህኒት ቤዛ ብለው እያሞገሱና እያቀፉ የሚደናገሩና የሚበዘበዙ ዜጎች ብዙ

መሆናቸውን ስናጤን ለሀቁ መጮህ በጣም አስፈላጊ መሆኑን እንገነዘባለን። ለእውነት እሞታለሁ አልሳሳም ለነፍሴ ተራ የዘፋኝ ስንኝ አይደለም። ለሀቅ ለመሞት መዘጋጀት ያስፈልጋል። የዝብር ቅርቅ ፖለቲካ አራማጆችን አስወግዶ ለሕዘብና ከሀገር መቆምን ማስቀደም አለብን። ሀፍረቱን በርካሽ ጨርቅ የሸፈነ ሁሉ ሐዋርያ እየመሰለን መደናገሩርን ማቆም አለብን። ነጋ ጠባ በጨለማ መመላለሱ መቆም አለበት። ተግሳፅን የሚወድ እውቀትን ይወዳል፤ ዘለፋን የሚጠላ ግን ደንቆሮ ነው ተብሏል። ዘለፋው ቀርቶ መለስተኛ ትችትም እያስቆጣ ባለበት በአሁኑ ጊዜ ሀቅን አንግሰን ወደፊት ማለት ግዴጃችን ነው። የቡችላነት፤ የሰጎንም ሆነ የእብድ ውሻንም ፖለቲካ መቃወም አለብን። ነጋ ጠባ ለቃላት ሸማኔዎች ሰለባ መሆን የለብንም። ሐሰተኛ ነቢዮችን ማወቅ መቻል አለብን። ፖለቲካ ክቡር  የሚሆነው ሕዝባዊ ይዘት ሲኖረው ብቻ ነው። ያለፈን ቁርሾና ቂም እያደሱ መታወክ ባይገባም ሰይጣን ቢያረምም ባሕታዊ አይመስልም መባሉን መርሳት አይገባን ም። ፖለቲካችን የሰከነ ፤ታሪክን ያልረሳ፤ ቅጥረኛነትን የተቃወመ ፤ነገን በአዲስ በዴሞክራሲ ሊገራ የታለመ መሆን አለበት። የወያኔ አገዛዝ ፀረ ኢትዮጵያ ነውና ለዚሁ አገዛዝ ማደር ወንጀል ነው። የወያኔ አገዛዝ ፀረ ሕዝብ ነውና ይህን ያለማየት ሰጎናዊ ፖለቲካ ሀገር አጥፊ ነው። የወያኔ አገዛዝ ዋና ጠላታችን ነውና ትኩረታችን በዋናው ጠላት መሆኑ ቀርቶ በሀቅ ለሀገር የቆሙትንና የሚታገሉትን ተቃዋሚ ድርጅቶችን መናከሱና ማውገዙም በጣም ጎጂ ነው።

" አፍ አላቸው አይናገሩምም
ዓይን  አላቸው አያዩምም
ጆሮ አላቸው አይሰሙምም
አፍንጫ አላቸው አያሸትሙምም
እጅ አላቸው አይዳሱስምም
እግር አላቸው አይሄዱምም
በጉሮረአቸው አይናገሩም"

ከመባል ያድነን።